አዋጅ ቁጥር …. /2018

**<u>የቁልፍ መሠረተ ልማቶች የሳይበር</u>**

**<u>ደህንነት አዋጅ</u>**

በቁልፍ መሠረተ ልማቶች ላይ የሚነጣጠሩ የሳይበር ጥቃቶች በሀገሪቱ ምጣኔ ሃብት፣ ማህበራዊ መስተጋብር፣ ብሔራዊ ደህንነት፣ ሰላምና መረጋጋት እንዲሁም ሉዓላዊነት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚፈጥሩ በመሆናቸው፤

በቁልፍ መሰረተ ልማቶች እና መሰረተ ልማቶቹ በሚይዟቸው ኢንፎርሜሽኖች እና ዳታዎች ላይ እየጨመሩ የመጡ የሳይበር ደህንነት ተጋላጭነቶችና ስጋቶችን መቀነስና መከላከል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ስጋትን መሠረት ያደረገ የቁልፍ መሠረተ ልማቶች ልየታ በማድረግ የሀገሪቱን ሀብት አቀናጅቶ ለመምራት የሚያስችል የሳይበር ደህንነት ጥበቃና ቁጥጥር ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ለቁልፍ መሰረተ ልማቶች የሳይበር ደህንነት ጥበቃ በባለድርሻ አካላት መካከል የተቀናጀ፣ ውጤታማና ፈጣን የመረጃ ልውውጥ እና የሳይበር ክስተቶችን ለማጋራትና ለመግታት የሚያስችል ስርዓት መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ውስብስብ፣ ተለዋዋጭ እና ከፍተኛ የሆነ ወድድር ባለበት የሳይበር ምህዳር ውስጥ የሚደረግ የሳይበር ደህንነትን የማረጋገጥ ተግባር ከፍተኛ የሆነ የካፒታል አቅምን የሚጠይቅ በመሆኑ፤ ለቁልፍ መሠረተ ልማቶች ጥበቃ የሚውል አስተማማኝ ሀገራዊ የፋይናንስ አቅም መፈጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ቁልፍ መሠረተ ልማቶችን በሚያስተዳድሩና የሳይበር ደህንነት ጥበቃን በሚያደርጉ አካላት ላይ ግልፅ ኃላፊነትና ተጠያቂነት መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥት አንቀጽ 55 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ “የቁልፍ መሰረተ ልማቶች የሳይበር ደህንነት አዋጅ ቁጥር … /2018” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. <u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠዉ ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ዉስጥ፤

1/ **“ቁልፍ መሰረተ ልማት”** ማለት ለሳይበር ጥቃት ከተጋለጠ በብሔራዊ ደህንነትና ብሔራዊ ጥቅሞች ላይ ጉዳት የሚያስከትል መሰረተ ልማት ወይም ተቋምን ያካትታል፤

2/ **"የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ስርዓት''** ማለት የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ምርቶች፣ አገልግሎቶች፣ ኔትወርኮች፣ የአሰራር ስርዓቶች፤ ሃርድዌሮችን፣ ሶፍትዌር መተግበሪያዎች ወይም ስልተ ቀመሮች ያካትታል፤

3/ **"የሳይበር ምህዳር''** ማለት እርስ በርሳቸው የተሳሰሩ የኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማቶች፣ ኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ስርዓቶች፣ ኢንፎርሜሽንን ወደ እውቀት የሚቀይርና የሚጠቀም የሰው ሃይል፤ እንዲሁም ተቋማዊና ማህበረሰባዊ ባህልን ያካተተ ምናባዊ ባህሪ ያለው ምህዳር ነው።

4/ **"የሳይበር ጥቃት"** ማለት በሳይበር ምህዳር የሚፈጸም ቁልፍ መሰረተ ልማት የማስተጓጎልን፣ ማቋረጥን፣ የማጥፋትን፣ ማፈንን፣ ያለፈቃድ ብርበራን፣ የመረጃ ስርቆትን፣ እንዲሁም የኢንፎርሜሽን ሚስጥራዊነት፣ ተደራሽነት ወይም ምልዑነትን የሚያሳጡ ጥቃቶችን ያካትታል።

5/ **"የቁልፍ መሰረተ ልማት ባለቤት"** ማለት የቁልፍ መሰረተ ልማት ባለቤት ወይም በቁልፍ መሰረተ ልማት ባለቤት መሰረተ ልማቱን እንዲያስተዳደሩ የተወከሉ ሰዎችን ይጨምራል፤

6/ **"ሀብት"** ማለት ካልተገባ ወይም ህገወጥ ተደራሽነት፣ ጥቅም፣ ይፋ መሆን፣ ለውጥ፣ ውድመት እና ተጋላጭነት ሊጠበቅ የሚገባው ማንኛውም የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ስርዓት ወይም ቁስ ነው፤

7/ **"የሳይበር ደህንነት ፕሮግራም"** ማለት በአደጋ ትንተና ላይ የተመሰረተ የሳይበር ደህንነትን ለማረጋገጥ እንዲተገበሩ የሚወጡ ስትራቴጂያ፣ የታክቲክ እና ኦፐሬሽናል እና የአሠራር እርምጃዎች እንዲሁም የአስተዳደር መዋቅሮችን ያጠቃልላል፤

8/ **"የሳይበር ደህንነት ማዕቀፍ"** ማለት አስተዳደሩ ወይም ቁልፍ መሰረተ ልማቶች እንዲያወጧቸው የሚጠበቁ የሳይበር ደህንነትን ለመምራት እና ለማስተዳደር የሚያስችሉ ስትራቴጂያዊ፣ የአተገባበር፣ የሂደት፣ የአሰራር ስርዓት፣ የስልት እና ሌሎች መሰል ሀገራዊ ወይም ዘርፍ ተኮር አስገዳጅ ወይም አስገዳጅ ያልሆኑ ማዕቀፎች ናቸው፤

9/ **"የሳይበር ደህንነት ፍተሻና ግምገማ"** ማለት የሳይበር ደህንነት ማዕቀፎች መሠረት ኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ስርዓቶችን የቅድመ ልማት፣ ቅድመ ግዥ እና ቅድመ ትግበራ ላይ የሚደረግ ፍተሻ እና ግምገማ የማድረግ ተግባር ነው፤

10/ **"የደህንነት ማረጋገጫ"** ማለት በቁልፍ መሰረት ልማት ውስጥ የሚሰራ ሰራተኛ ወይም ኃላፊ ለታጨበት ወይም ለተመደበበት የስራ ሃላፊነት፣ አስፈላጊ ሙያዊ ስብዕና እና ስነ-ምግባር ያለው መሆኑን የማጥናትና የማጣራት ሂደት ነው፤

11/ **"የሳይበር ደህንነት ኦዲት"** ማለት በቁልፍ መሰረተ ልማቶች ላይ ተጋላጭነትን ለማወቅ የዘልቆ ገብ ፍተሻ ተግባራትን ማከናወን እና ሀገራዊ

የሳይበር ደህንነት ማዕቀፎችን መሠረት በማድረግ የቁልፍ መሰረተ ልማቶችን የሳይበር ደህንነት ስርዓት በመገምገም እንደአስፈላጊነቱ የእርምት እርምጃዎች እንዲወስዱ ማድረግን ይጨምራል፤

12/ **“ብሔራዊ ደንገተኛ የኮምፒውተር አደጋ ምላሽ መስጫ ማዕከል”** ማለት በቁልፍ መሰረተ ልማቶች ላይ የሚሰነዘር ጥቃትን ለመከላከል እንዲቻል የጥቃት አደጋዎችን አስቀድሞ የመለየት፣ የመተንተን፣ ዜጎችንና ተቋማትን የማስጠንቀቅ፣ መወሰድ ስለሚገባቸው እርምጃዎች ምክርን የማቅረብ፣ የማገገሚያ መንገዶችን የመዘየድ እና በዚህ ዘርፍ ሀገራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ቅንጅትን እንዲፈጠር የማስቻል ተግባራትን የሚያከናውን ማዕከል ነው፤

13/ **“የሳይበር ደህንነት አገልግሎት ሰጪ”** ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የሳይበር ደህንነት ምርት ወይም አገልግሎት ለመስጠት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ነው፤

14/ **“የሳይበር ደህንነት ባለሙያ”** ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የሳይበር ደህንነት ተግባራትን እንዲያከናውን እውቅና የተሰጠው ሰው ነው፤

15/ **"የሳይበር ደህንነት ምርትና አገልግሎት"** ማለት የሳይበር ጥቃትን ወይም የኢንፎርሜሽንን ሚስጥራዊነት፣ ምልዑነት እና ተደራሽነት ስጋቶችን ለመቀነስ እና ለማስተዳደር የሚሰጡ ምርቶች ወይም አገልግሎት ነው።

16/ **“የመንግስት አስተዳደር አካል”** ማለት በሙሉ ወይም በከፊል በመንግስት በጀት የሚተዳደር ተቋም ነው።

17/ **“አስተዳደር”** ማለት የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ነዉ፤

18/ “ሰዉ” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰዉነት መብት የተሰጠዉ አካል ነዉ፤

19/ ማንኛዉም በወንድ ፆታ የተገለፀው ሴትንም ይጨምራል።

## 3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ አዋጅ ቁልፍ መሰረተ ልማት ተብለው በተለዩ መሰረተ ልማቶች እና የሳይበር ደህንነት ምርት ወይም አገልግሎት በሚያቀርቡ ሰዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

## ክፍል ሁለት

## ቁልፍ መሰረተ ልማቶችን ስለመለየትና ስለመጠበቅ

## 4. <u>የቁልፍ መሰረተ ልማት ዘርፎች፤</u>

1/ የሚከተሉት የቁልፍ መሰረተ ልማት ዘርፎች ተብለው በዚህ አዋጅ ተለይተዋል፡

ሀ) የኢንፎርሜሽን እና ኮሙኒኬሽን፤
ለ) የፋይናንስ፤
ሐ) የፀጥታና ደህንነት፤

መ) የትራንስፖርት፤

ሠ) የትምህርት፤

ረ) የጤና፤

ሰ) የውሃና ኢነርጂ፤

ሸ) የመንግሥት አገልግሎቶች፤

ቀ) የአደጋ መከላከል አገልግሎቶች፤

በ) ግብርና፤

ተ) ንግድ እና ኢንዱስትሪ፤

2/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 እንደተጠበቀ ሆኖ አስተዳደሩ ተጨማሪ ቁልፍ መሰረተ ልማት ዘርፎችን ሊለይ ይችላል፤

3/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት ቁልፍ መሠረተ ልማትን ለመለየት የሚከተሉት ዝቅተኛ መስፈርቶች መሟላት ይኖርባቸዋል፦

ሀ) የሳይበር ጥቃት ቢደርስበት በምጣኔ ሀብት፣ ማህበራዊ መስተጋብር፣ በማህበረሰቡ የዕለት ተዕለት ኑሮ ላይ ከፍተኛ አደጋ የሚጥል ሲሆን፤

ለ/ የሳይበር ጥቃት ቢደርስበት በብሔራዊ ደህንነት፣ በሰላምና መረጋጋት፣ በዲፕሎማሲ ወይም ሀገራዊ ገፅታ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድር ሲሆኑ፤ እና

ሐ) ከፍተኛ ትስስርና መስተጋብር ያላቸውና ጉዳት ቢደርስበት ወደ ሌሎች ቁልፍ መሰረተ ልማት ዘርፎች የሚዛመት ሲሆኑ፤

መ) ሌሎች እንደአስፈላጊነቱ አስተዳደሩ በመመሪያ በሚያወጣቸው አግባብነት ያላቸው መስፈርቶች።

## 5. <u>ቁልፍ መሰረተ ልማቶችን ስለመሰየም</u>

1/ አስተዳደሩ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 4 መሠረት የተለዩ ቁልፍ መሠረተ ልማት ዘርፎች ውስጥ ለሳይበር ጥቃት ተጋላጭ የሆኑ እና በዚህ አዋጅ መሠረት ጥበቃ ሊደረግላቸው የሚገቡ የቁልፍ መሰረተ ልማቶችን በመለየት በመመሪያ ይሰይማል፤ ለሚመለከተው የመሰረተ ልማቱ አስተዳደሩ ያሳውቃል፤

2/ አስተዳደሩ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት ቁልፍ መሰረተ ልማት ሲሰይም፤ የሳይበር ደህንነት ማዕቀፎችንና ምርጥ ተሞክሮዎችን መሠረት ያደርጋል፤ የሀገሪቱን የሳይበር ደህንነት ስጋት ተፅዕኖ ይተነትናል፤ ይገመግማል፤ እንዲሁም ወቅታዊ ፍላጎትን መሠረት ያደርጋል፤

3/ በዚህ አንቀፅ መሠረት በቁልፍ መሠረተ ልማትነት የተለየ ተቋም በአዋጁ መሠረት የሚሰጡ የሳይበር ደህንነት ጥበቃ ተግባራት ተጠቃሚ ይሆናል።

## 6. <u>ከቁልፍ መሰረተ ልማትነት ስለመሰረዝ</u>

1/ ቁልፍ መሠረተ ልማት ተብሎ የተሰየመ መሰረተ ልማት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀፅ 3 ላይ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ማሟላት ሲያቆም

አስተዳደሩ ተገቢውን ግምገማ በማድረግ ከቁልፍ መሰረተ ልማትነት ሊሰርዘው ይችላል፤

2/ ከቁልፍ መሰረተ ልማትነት ለተሰረዘ መሰረተ ልማት በዚህ አዋጅ መሠረት የሚደረገው ጥበቃ ይቋረጣል።

## 7. <u>የቁልፍ መሰረተ ልማት ባለቤት ግዴታ</u>

ማንኛውም የቁልፍ መሰረተ ልማት ባለቤት የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፤

1/ ሀገራዊ የሳይበር ደህንነት ማዕቀፎች መሠረት በማድረግ የራሱን የሳይበር ደህንነት ፕሮግራሞችን የመቅረፅ፤

2/ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚወጡ ወይም እንደ ሀገር እውቅና የተሰጣቸውን ዓለም አቀፍ አስገዳጅ የሳይበር ደህንነት ማዕቀፎች ተግባራዊ የማድረግ፤

3/ በሀገራዊ ህጎችና ፖሊሲዎች እንዲሁም በአስተዳደሩ በሚወጡ ቴክኒካል ፖሊሲ መሠረት ያደረገ የራሱን የሳይበር ደህንነት ማዕቀፍ ማዘጋጀትና ተግባራዊ የማድረግ፤

4/ አስተዳደሩ በሚያወጣው ስታንዳርድ መሰረት በስሩ የሚያስተዳድራቸውን ሀብቶች የመመደብና የመጠበቅ፤

5/ አስተዳደሩ በሚዘረጋው ስርዓት መሠረት ወቅታዊ የሳይበር ደህንነት የአደጋ ዳሰሳ እና የተፅዕኖ ትንተና ማድረግ፤

6/ አስተዳደሩ በየአመቱ በሚያከናውነው ሀገራዊ የሳይበር ደህንነት የአደጋ ዳሰሳ ላይ የመሳተፍና አስፈላጊ መረጃዎችን የማቅረብ፤

7/ አስተዳደሩ በሚዘረጋው ስርዓት መሠረት የሳይበር ኦዲት እና የሳይበር ፍተሻና ግምገማ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት የመያዝና የማሳደስ፤

8/ በሳይበር ኦዲት ወይም የሳይበር ደህንነት ፍተሻና ግምገማ ግኝት መሠረት በሚሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ተገቢውን የእርምት እርምጃ የመውሰድ፤

9/ በሀገራዊ የሳይበር ደህንነት ማዕቀፍ መሠረት አስፈላጊውን የሳይበር ደህንነት አደረጃጀት የመፍጠር፣

10/ ከአስተዳደሩ የተሰጡ ወይም በአስተዳደሩ እውቅና የተሰጣቸው የሙያ ሰርተፍኬቶችን ያገኙ የሳይበር ደህንነት ባለሙያዎችን የመቅጠር፤ ያሉትን ባለሙያዎች አስተዳደሩ በሚዘረጋው ስርዓት መሠረት የሙያ ብቃት ማረጋገጫ እንዲያገኙ የማድረግ፤

11/ ጥቅም ላይ የሚያውሏቸውን የቴክኖሎጂ ምርቶች አቅርቦት ሰንሰለት ደህንነት ማረጋገጥ፤

12/ አዳዲስ ወይም ተሻሽለው የሚቀርቡ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ስርዓቶችን በግዥ፣ በስጦታ፣ በማልማት ወይም በማንኛውም መልኩ አግኝተው ከመተግበራቸው በፊት አስተዳደሩ በሚዘረጋው ስርዓት መሠረት ደህንነት ማረጋገጫ የማግኘት፤

13/ አስተዳደሩ በሚዘረጋው ስርዓት መሠረት የሳይበር ጥቃቶችን ክትትል፣ ሪፖርት እና ምላሽ የማድረግ እና ተግባሩን የሚያስተዳድር ማዕከል የማደራጀት፣

14/ የሳይበር ክስተት ማጋጠሙን እንዳወቀ በ48 ሰዓታት ውስጥ ለብሔራዊ ደንገተኛ የኮምፒውተር ምላሽ መስጫ ማዕከል የማሳወቅ፤ እና የሚሰጠውን አስገዳጅ ምክረ ሃሳቦች ወይም አቅጣጫዎችን በሚሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ የመተግበር፤

15/ አስተዳደሩ በሚዘረጋው ስርዓት መሰረት በየወቅቱ አስፈላጊ ኢንፎርሜሽኖችን የመለዋወጥ፤

16/ የሳይበር ደህንነት ልምምድና ስልጠና ፕሮግራሞችን የማዘጋጀትና የመተግበር እንዲሁም አስተዳደሩ በሚያመቻቸው ልምምድና ስልጠናዎች ላይ የመሳተፍ፤

17/ የቁልፍ መሠረተ ልማቱ ሀብቶች ተደራሽ የሚሆኑላቸው ሠራተኞችን ወይም ኃላፊዎች በሚመለከተው የመንግሥት አካል የደህንነት ማረጋገጫ እንዲያገኙ የማድረግ፤

18/ የሳይበር ደህንነት የሚጠይቀውን የሙያ ስነ-ምግባር መከበሩን የማረጋገጥ።

## 8. ውክልና ስለመስጠት

1/ የቁልፍ መሰረተ ልማት ባለቤቶች በዚህ አዋጅ አንቀፅ 7 የተደነገጉ ግዴታዎች እንደአግባብነቱ በራስ አቅም ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት ፈቃድ በተሰጠው የሳይበር ደህንነት አገልግሎት አቅራቢ ሰው ውክልና በመስጠት ተግባራዊ ሊያደርግ ይችላል።

2/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 ቢኖርም አስተዳደሩ ከብሔራዊ ደህንነትና ጥቅም አንፃር በውክልና የሳይበር ደህንነት አገልግሎት የማይሰጥባቸውን የቁልፍ መሰረተ ልማቶች በመመሪያ ይለያል።

## 9. ፈንድ ስለማቋቋም

የቁልፍ መሰረተ ልማቶችን ደህንነት ለማስጠበቅ የሚዘረጉ የሳይበር ደህንነት ፕሮግራሞችን እና የሳይበር ደህንነት ማዕቀፎችን ለማስተግበር የሚያስችል የቁልፍ መሰረተ ልማቶች የሳይበር ደህንነት ፈንድ ተቋቁሟል፤ ዝርዝሩ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል።

# ክፍል ሦስት
# የቁልፍ መሰረተ ልማቶች ሳይበር ደህንነት ስርዓት

## 10. የአስተዳደሩ ስልጣንና ተግባር

አስተዳደሩ ከቁልፍ መሰረተ ልማት የሳይበር ደህንነት ጋር በተገናኘ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1/ ሳይበር ደህንነት አስተዳደር ጉዳይን በተመለከተ፦

ሀ) አስገዳጅ ሀገራዊ የሳይበር ደህንነት ፕሮግራሞችን ይቀርጻል፤ አፈፀማቸውን ይከታተላል፤

ለ) ቁልፍ መሰረተ ልማቶች የሚያወጧቸው የሳይበር ደህንነት ፕሮግራሞች፤ ሀገራዊ የሳይበር ደህንነት ማዕቀፍን ተከትለው መዘጋጀታቸውንና መተግበራቸውን ይከታተላል፣ ይደግፋል፤

ሐ) ሀገራዊ የሳይበር ደህንነት ማዕቀፍ ትግበራ ሂደትን ይከታተላል፤ ያስፈፅማል፤

መ) ሀገራዊ የሳይበር ደህንነት አደጋ እና የደህንነት ቁመና ደረጃ ዳሰሳ ሪፖርት በየዓመቱ ያዘጋጃል፤

ሠ) ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የሳይበር ደህንነት ልምምዶችን፣ ስልጠናዎችን እና የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞችን ያዘጋጀል ይተገብራል፤

ረ) በቁልፍ መሰረተ ልማቶች ደህንነትና አይበገሬነት ለመፍጠር የሚያስችል ሀገራዊ የሳይበር ደህንነት ፎረም ይመሰርታል፤ ያስተዳድራል፤

ሰ) የሚያወጣቸውን የሳይበር ደህንነት ማዕቀፎችን፣ የአሰራር ስርዓቶች፣ አስፈላጊ መረጃዎችን የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ተደራሽ ያደርጋል፡፡

2/ ስለሳይበር ክስተቶች ምላሽ አሰጣጥ በተመለከተ፦

ሀ) በቁልፍ መሰረተ ልማቶች ላይ ጥቃቶች እንዳይደርሱ ተገቢውን የቅድመ መከላከል እና ጥቃቶች ሲደርሱ ምላሽ የሚሰጥበትን ስርዓት ይዘረጋል፤

ለ) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በቁልፍ መሰረተ ልማቶች ላይ የሳይበር ጥቃቶች ለመከላከል ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፤

ሐ) በቁልፍ መሰረተ ልማቶች ላይ የሚደርሱ የሳይበር ክስተቶች የመረጃ ልውውጥና የቅድመ ማስጠንቀቂያ ያወጣል፤

መ) የሳይበር ክስተቶችን በመከላከል ዙሪያ ሀገር አቀፍ፣ ቀጠናዊ፣ አህጉራዊ ወይም ዓለምአቀፋዊ የትብብርና የትስስር ግንኙነቶችን ያስተባብራል በበላይነት ይመራል፤

ሠ) በቁልፍ መሰረተ ልማት የሳይበር ክስተት ክትትል ሪፖርት እና ምላሽ እንዲሰጡ የሚቋቋሙ አደረጃጀቶች የዘረጓቸውን የአሰራር ስርዓቶች እና አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ ቅንጅታዊ አሰራር ስርዓት በመመሪያ ይዘረጋል፡፡

3/ የሳይበር ደህንነት ኦዲትና የሳይበር ደህንነት ፍተሻና ግምገማ በተመለከተ

ሀ) ሀገራዊ የሳይበር ደህንነት ማዕቀፎችን መሠረት በማድረግ ቁልፍ መሠረተ ልማቶችን ቢያንስ በየዓመቱ መደበኛ እና በማንኛውም ጊዜ ድንገተኛ የሳይበር ደህንነት ኦዲት ሊያደርግ ይችላል፤ ተፈላጊ መስፈርቶቹን ለሚያሟሉ የሳይበር ደህንነት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ይሰጣል፤

ለ) ሀገራዊ የሳይበር ደህንነት ማዕቀፎችን እና ዓለም አቀፍ ስታንዳርዶችን መሠረት በማድረግ ቁልፍ መሠረተ ልማቶች የሳይበር ደህንነት ፍተሻና ግምገማ ያደርጋል፤ ፈቃድ ይሰጣል፤

ሐ) በዚህ አንቀፅ ንዑስ 1 እና 2 መሠረት የሚደረጉ የሳይበር ደህንነት ኦዲት እና የሳይበር ደህንነት ፍተሻና ግምገማዎችን በውክልና እንዲያደርጉ ለግል አገልግሎት ሰጪዎች ፈቃድ ይሰጣል፤

መ) የሳይበር ደህንነት ኦዲት እና የሳይበር ደህንነት ፍተሻና ግምገማ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ይሰጣል፤ ሰርተፍኬቱ ስለሚሰጥበት እና እድሳት ስለሚደረግበት አግባብ በመመሪያ ይወሰናል፤

## 11. ስለ አገልግሎት ክፍያ

አስተዳደሩ ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ መሰረት ክፍያዎችን ይሰበስባል፡፡

# ክፍል አራት
# ስለሳይበር ደህንነት አገልግሎት ሰጪዎች

## 12. ለሳይበር ደህንነት አገልግሎት ሰጪዎች ፈቃድ

1/ አስተዳደሩ የሳይበር ደህንነት አገልግሎትን ለመስጠት የሚያስችል ፈቃድ ይሰጣል፤

2/ ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት በአስተዳደሩ የሚሰጠው ፈቃድ ሳይኖረው የሳይበር ደህንነት ምርት ወይም አገልግሎቶችን መስጠት አይችልም፤

3/ አስተዳደሩ ፈቃድ የሚያስፈልጋቸውን የሳይበር ደህንነት ምርትና አገልግሎት ዓይነቶችን፣ ፈቃድ ለማግኘት ስለሚቀርብ ማመልከቻ ሥርዓት፣ ስለፈቃድ ይዘት፣ ምላሽ ስለሚሰጥበት፣ ፍቃድ ስለሚታደስበት፣ ቅሬታ ስለሚቀርብበት እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ጉዳዮች አስመልክቶ ዝርዝሩን በደንብና መመሪያ ይወሰናል፡፡

## 13. ፈቃድ የሚሰጥባቸው ዋና መስፈርቶች

በዚህ አዋጅ አንቀፅ 12 መሠረት ፈቃድ ለማግኘት የሚያመለክት ሰው የሚከተሉትን ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላት ይኖርበታል፦

1/ የሕግ ሰውነት ማረጋገጫ ወይም መቋቋሚያ ሰነድ፤

2/ ተገቢውን የደህንነት ማረጋገጫ ያሟላ፤

3/ ዝርዝሩ በመመሪያ የሚወሰን ሆኖ አገልግሎቱን ለመስጠት የሚያስችል ባለሙያዎች፣ ቴክኖሎጂ፣ የአሰራር ስርዓት እና ካፒታል፤

4/ በኢትዮጵያ ቋሚ አድራሻ፤

5/ በፍርድ ወይም በሕግ ችሎታውን ያላጣ፤

6/ በማጭበርበር፣ ሙስና ወይም ከእምነት ማጉደል ጋር ተያያዥ በሆኑ ወንጀሎች ተፈርዶበት የማያውቅ፤ ወይም የተሰየመ፤ እና

7/ ፈቃድ እንደሚሰጥበት የሳይበር ደህንነት አገልግሎት አስተዳደሩ በመመሪያ የሚያወጣቸው ዝርዝር መስፈርቶችን፡፡

**14. ፈቃድ የተሰጠው ሰው ግዴታ**

በዚህ አዋጅ መሠረት ፈቃድ የተሰጠዉ ማንኛዉም ሰዉ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

1/ የተሰጠውን ፈቃድ ለተፈቀደለት ዓላማ እና ወሰን ብቻ የመጠቀም፤

2/ የተሰጠዉን ፍቃድ ለሦስተኛ ወገን በማናቸውም መልኩ አስተዳደሩን ሳያሳውቅና ፈቃድ ሳያገኝ ያለማስተላለፍ፤ ያለማዋስ፣ እንዲጠቀምበት ያለማድረግ፤

3/ ለፈቃዱ መሰጠት አስፈላጊ የሆኑ መስፈርቶች ላይ ለውጥ ሲኖር ለአስተዳደሩ ወዲያውኑ የማሳወቅ፤

4/ በስራ አጋጣሚ ያገኛቸውን መረጃዎች በሚስጥር የመያዝ፤

5/ አስተዳደሩ የቁጥጥር ኃላፊነቱን በሚወጣበት ወቅት የሚጠይቃቸውን አስፈላጊ መረጃዎች የማቅረብና ለሚያነሳቸው ጥያቄዎች ተገቢውን ትብብር የማድረግ፤ እና

6/ ይህን አዋጅ እና አዋጁን ለማስፈፀም የሚወጡ ደንቦች እና መመሪያዎች ላይ የተቀመጡ ሌሎች ግዴታዎች ማክበር፡፡

**15. ፈቃድ ስለመሰረዝ**

በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠ ፈቃድ ከሚከተሉት ሁኔታዎች በአንዱ ሊሰረዝ ይችላል፤

1/ ፈቃዱን ለማግኘት የቀረቡ መረጃዎች የተጭበረበሩ ወይም ሀሰተኛ ሆነው ሲገኙ፤

2/ የተሰጠውን ፈቃድ ከተሰጠው ዓላማና ወሰን ውጪ ጥቅም ላይ እየዋለ መሆኑ ሲረጋገጥ፤

3/ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ይህን አዋጅ እና አዋጁን ለማስፈፀም የሚወጡ ደንብና መመሪያዎች ላይ የተደነገጉ ስርዓቶች ላይ ጥሰቶችን መፈፀሙ ሲረጋገጥ፤

4/ የተሰጠው ፈቃድ የጊዜ ገደብ ሲያበቃ እና ሳይታደስ ሲቀር፤

5/ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ሲሞት ወይም በሕግ ወይም በፍርድ ችሎታውን ሲያጣ፤ ወይም ፈቃድ የተሰጠው ድርጅት ሲፈርስ፣ በህግ መክሰሩ ሲረጋገጥ ወይም ሲዘጋ፤

6/ ፍቃድ የተሰጠው ሰው በማጭበርበር፣ በማታለል ወይም እምነት በማጉደል ወንጀል ተከሶ የተፈረደበት ከሆነ፤

7/ ፈቃዱን ለማግኘት ከሚያስፈልጉ መስፈርቶች ውስጥ አንዱ ሲጓደል፤ወይም

8/ ባለፈቃዱ አገልግሎት መስጠቱን ሲያቋርጥ እና ፈቃዱን ሲመልስ።

## 16. ፈቃድ ስለማገድ

1/ አስተዳደሩ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 15 የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ስለመኖራቸው ጥርጣሬ በሚኖርበት ወቅት ጉዳዩ እስኪጣራ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ፈቃዱ እስከ ስልሳ ተከታታይ ቀናት ድረስ እንዲታገድ ሊወስን ይችላል፤

2/ አስተዳደሩ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት በሚያደርገው ማጣራት የተጠረጠሩ ጥፋቶች መፈፀማቸውን ካረጋገጠ ፈቃዱን ይሰርዛል፤ ወይም እንደ ጥፋቱ ክብደት በማስጠንቀቂያ ሊያልፍ ይችላል፤ ጥፋቱን መፈፀሙ ካልተረጋገጠ ባለፈቃዱ ስራውን እንዲጀምር ይፈቀዳል።

## 17. ለባለሙያዎች የሙያ ማረጋገጫ ወይም እውቅና መስጠት

አስተዳደሩ በቁልፍ መሰረተ ልማቶች ውስጥ የሳይበር ደህንነት ተግባር ለሚያከናውኑ የሳይበር ደህንነት ባለሙያውች የሙያ ማረጋገጫ ወይም እውቅና ምስክር ወረቀት የሚሰጥበት ስርዓት በደንብና መመሪያ ይዘረጋል።

# ክፍል አምስት
# ስለአስተዳደራዊ እርምጃ እና ቅሬታ አቀራረብ ስርዓት

## 18. አስተዳደራዊ እርምጃ

1/ የመንግስት አስተዳደር አካላትን ሳይጨምር ማንኛውም የቁልፍ መሰረተ ልማት ባለቤት በዚህ አዋጅና አዋጁን ለማስፈፀም የሚወጡ ደንብና መመሪያ በመጣስ ሆን ብሎ፦

ሀ) አስገዳጅ የሳይበር ደህንነት ማዕቀፎችን በወቅቱ ካልተገበረ ከአምስት መቶ ሺህ እስከ አንድ ሚሊዮን ብር፤

ለ) የሚያጋጥሙ የሳይበር ደህንነት ክስተቶችን ለብሔራዊ ድንገተኛ የኮምፒውተር አደጋ ምላሽ መስጫ ማዕከል በ48 ሰዓታት ውስጥ ካላሳወቀ ወይም ተገቢውን የእርምት እርምጃ ሳይወስድ ከቀረ ከአንድ ሚሊዩን አምስት መቶ ሺህ እስከ ሁለት ሚሊዮን ብር፤

ሐ) ብሔራዊ ድንገተኛ የኮምፒውተር አደጋ ምላሽ መስጫ ማዕከል ለሳይበር ጥቃቶች ምላሽ ለመስጠት በሚያደርገው እንቅስቃሴ አስፈላጊ መረጃዎችን ካልሰጠ ወይም ተገቢውን ትብብር ካላደረገ ከሦስት መቶ ሺህ እስከ አምስት መቶ ሺህ ብር፤

መ) በየጊዜው ለሚደረገው የሳይበር ደህንነት ኦዲት ተገቢውን ትብብር ካላደረገ፤ ከአንድ ሚሊዩን አምስት መቶ ሺህ እስከ ሁለት ሚሊዮን፤

ሠ) በሳይበር ኦዲት የተገኙ ክፍተቶች ላይ አስተዳደሩ ማስተካከያ እንዲያደርግ በተሰጠው አቅጣጫ መሠረት ተገቢውን የእርምት እርምጃ በወቅቱ ካልወሰደ ከስምንት መቶ ሺህ እስከ አንድ ሚሊዮን ብር፤

ረ) የሳይበር ደህንነት ፍተሻና ግምገማ ያልተደረገባቸውን የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ስርዓቶችን በማናቸውም መልኩ ከተጠቀመ፤ ከስምንት መቶ ሺህ ብር እስከ አንድ ሚሊየን ብር

አስተዳደራዊ መቀጮ ይቀጣል።

2/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) የተደነገጉ ጥፋቶች በቸልተኝነት የተፈፀሙ ከሆነ እንደ ጥፋቱ ዓይነት በንዑስ አንቀፁ ከተደነገጉ አስተዳደራዊ የገንዘብ መቀጮዎች ከግማሽ ባልበለጠ ይቀጠል።

3/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ (1) እና (2) የተደነገገው ቢኖርም የደረሰው ጉዳት አነስተኛ ከሆነ ወይም በተደጋጋሚ ያልተፈፀመ ከሆነ አስተዳደሩ ተገቢው የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ሊያልፈው ይችላል፤

4/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ (1) የተደነገገው ቢኖርም ቀልፍ መሰረተ ልማት ተብለው በተለዩ የመንግስት አስተዳደር መስሪያ ቤት የሳይበር ደህንነት ላይ የተመደበ ሀላፊ ወይም ሰራተኛ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተቀመጡትን ድርጊቶች ከፈፀመ ወይም እንዲፈፀሙ ካደረገ ከብር ሃምሳ ሺህ እስከ ብር አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።

5/ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ አንቀፅ 12 ንዑስ አንቀፅ 2 በመተላለፍ የፀና ፈቃድ ሳይኖረው የሳይበር ደህንነት አገልግሎት የሰጠ እንደሆነ ወይም በአንቀፅ 14 የተደነገጉ ግዴታዎችን ተላልፎ ከተገኘ ከብር አንድ ሚሊዩን ሁለት መቶ ሺህ ብር እስከ ሁለት ሚለዮን ብር ይቀጣል፤

6/ በዚህ አንቀፅ የተዘረዘሩ ጥፋቶችን የቁልፍ መሰረተ ልማት ባለቤቱ ወይም የሳይበር ደህንነት አገልግሎት የሚሰጠ አካል ከአንድ ጊዜ በላይ የፈጸመ እንደሆነ ለጥፋቱ የተጠቀሰውን ትልቁን የገንዘብ መጠን በሶስት እጥፍ እንዲከፍል ይደረጋል።

7/ አስተዳደሩ በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚጣሉ አስተዳደራዊ ቅጣቶችን ያስፈፅማል።

8/ በዚህ አንቀፅ ስር የተመላከቱ የአስተዳደራዊ የገንዘብ ቅጣቶች እንደ አስፈላጊነቱ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ሊሻሻሉ ይችላሉ።

## 19. የቅሬታ አፈታት

1/ ማንኛውም ቁልፍ መሰረተ ልማት ወይም ሰው ከዚህ አዋጅ እና አዋጁን ተከትለው ከሚወጡ ደንብ፣ መመሪያ ወይም ስታንዳርዶች አፈፃፀም ጋር በተያያዘ ለሚኖረው ማንኛውም አይነት ቅሬታ የቅሬታው መንስዔ ከታወቀበት በኋላ ባሉት ተከታታይ 30 ቀናት ውስጥ አቤቱታውን ለአስተዳደሩ በፅሑፍ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

2/ አስተዳደሩ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት የቀረበለትን አቤቱታ ከቀረበለት በ15 ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ አስፈላጊውን ውሳኔ መስጠት ይኖርበታል፤ ዝርዝር የቅሬታ አቀራረብ ስርዓቱ በአስተዳደሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

3/ አስተዳደሩ በሰጠው ውሳኔ ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን የሚያስተናግድ ከሚመለከታቸው አካላት የተውጣጣ ቦርድ በደንብ ይቋቋማል፤ ቦርዱ ቅሬታ የሚያስተናግድበት ስርዓት በደንብ ይወሰናል፡፡ ቦርዱ በሰጠው ውሳኔ ያልረካ ማንኛውም ሰው አቤቱታውን በ60 ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ አግባብነት ላለው ፍርድ ቤት ሊያቀርብ ይችላል፡፡

## ክፍል ስድስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 20. የመተባበር ግዴታ

ማንኛዉም ሰው አስተዳደሩ በዚህ አዋጅ የተሰጡትን ኃላፊነቶች ለመወጣት የሚወስዳቸውን እርምጃዎች የማክበርና የመተባበር ግዴታ ይኖርበታል፡፡

## 21. የወንጀል ተጠያቂነት

1/ በቁልፍ መሰረተ ልማት የሳይበር ደህንነት ላይ የተመደበ ሀላፊ ወይም ሰራተኛ ይህን አዋጅ በመጣስ ሆን ብሎ፦

ሀ) አስገዳጅ የሳይበር ደህንነት ማዕቀፎችን በወቅቱ ካልተገበረ ወይም መተግበሩን ካላረጋገጠ፤

ለ) የሚያጋጥሙ የሳይበር ጥቃቶች ለብሔራዊ ድንገተኛ የኮምፒውተር አደጋ ምላሽ መስጫ ማዕከል በ48 ሰዓታት ውስጥ ካላሳወቀ ወይም ተገቢውን የእርምት እርምጃ ሳይወስድ ከቀረ፤

ሐ) በሳይበር ኦዲት የተገኙ ክፍተቶች ላይ አስተዳደሩ ማስተካከያ እንዲያደርግ በሰጠው አቅጣጫ መሠረት ተገቢውን የእርምት እርምጃ በወቅቱ ካልወሰደ፤

መ) የሳይበር ደህንነት ፍተሻና ግምገማ ያልተደረገባቸውን የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ስርዓቶችን በማናቸውም መልኩ ከተጠቀመ ወይም ጥቅም ላይ እንዲውሉ ካደረገ፤

እስከ አንድ አመት በሚደርስ ቀላል እስራት ይቀጣል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ላይ የተደነገገው ወንጀል የቁልፍ መሰረተ ልማት አገልግሎትን ያቋረጠ ወይም ያስተጓጎለ ወይም ጉዳት ያደረሰ ወይም ተዓማኒነቱን ያሳጣ ወይም ሚስጥራዊነቱን ያጋለጠ ወይም በሀገር ደህንነት ወይም ጥቅም ወይም በዜጎች ጤና ወይም ህይወት ወይም በከባቢ አየር ላይ ጉዳት ያደረሰ ከሆነ በቁልፍ መሰረተ ልማት የሳይበር ደህንነት ላይ የተመደበው ሀላፊ ወይም ሰራተኛ ከሰባት ዓመት እስከ አስር ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

3/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው የወንጀል ድርጊት በቸልተኝነት የተፈፀመ ከሆነ ቅጣቱ እንደአግባብነቱ እስከ ስድስት ወር በሚደርስ ቀላል እስራት ይሆናል፡፡

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተጠቀሰው የወንጀል ድርጊት የተፈፀመው በቸልተኝነት ከሆነ ቅጣቱ እንደአግባብነቱ ከሦስት እስከ አምስት ዓመት የሚደርስ ጽኑ እስራት ይሆናል፡፡

## 22. ተፈፃሚ ስለማይሆኑ ሕጎች

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

## 23. ደንብና መመሪያ ስለማውጣት

1/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

2/ አስተዳደሩ በዚህ አዋጅና በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 24. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ከአንድ አመት በኃላ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ……………. ቀን 2018 ዓ.ም

**አዲስ አበባ……ቀን……………2018 ዓ.ም**

**ታዬ አፅቀስላሴ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ፕሬዘዳንት**